# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
## ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ሁለተኛ አስቸኳይ ጉባዔ ውሳኔዎች

### I. አጠቃላይ፤

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) አስቸኳይ ሁለተኛ ጉባዔ ከጥር ፭ ቀን እስከ ጥር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ. ም. (January 13-16, 2006) ለአራት ቀናት በአሜሪካ አገር ሜሪላንድ ውስጥ ተካሄዷል።

ይኸ የኢዴኃኅ ብሔራዊ ሸንጎ ሁለተኛ አስቸኳይ ጉባዔ የተጠራው የኢሕአዴግ አገዛዝ በሕዝባችን ላይ እየፈጸመ ያለው ግድያና አፈና፥ ወከባና ጭፍጨፋ ከምን ጊዜውም በላይ ተባብሰው ባሉበት፥ የሕግ የበላይነትና የመብት መከበር ደብዛቸው ጠፍቶ አረመኔያዊ የሽብር አገዛዝ ተስፋፍቶ በሚገኝበት፥ ሕዝባችን ለመብቱ መከበርና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን እያካሄደ ያለው ትግል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠነከረና እየጎለበተ ሄዶ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በሚገኝበት ወቅት ነው።

የኢዴኃኅ ብሔራዊ ሸንጎ ሁለተኛ መደበኛ ጉባዔ በተካሄደ በአምስት ወራት ጊዜ ውስጥ ይኸ አስቸኳይ የሸንጎ ጉባዔ የተጠራበት ዋናው ምክንያት ፈጣን ለውጦችን እያሳየ ያለውን የአገራችንን የፖለቲካ ሁኔታ በጥልቀት በመገምገም አጠቃላይ የጋራ ግንዛቤዎችና ስምምነቶች ላይ ለመድረስ፥ እንዲሁም በኅብረቱ ውስጥ የተፈጠሩ ችግሮችን በመርመርና ለችግሮቹ ተገቢና ወቅታዊ መፍትሔ በመስጠት ከጊዜ ወደ ጊዜ እድገትና ጥንካሬ አግኝቶ በመቀጣጠል ላይ የሚገኘውን የሕዝብ ትግል ከግብ ለማድረስ አስፈላጊና ተገቢ የሆኑ ፖሊሲዎችን ለማውጣትና የትግል ስትራቴጂዎችን ለመቀየስ ነው።

ለአራት ቀናት ሲካሄድ የቆየው ይኸ የኢዴኃኅ ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) አስቸኳይ ጉባዔ ከኅብረቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፥ ከኅብረቱ ጽ/ቤቶችና ከተግባር ኮሚቴዎች የቀረቡ የሥራ ዘገባዎችን አዳምጧል። በአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ላይ ሰፊ ውይይቶችን በማከሄድና እንዲሁም ኅብረቱ ባለፉት አምስት ወራት ያከናወናቸውን ተግባሮችና የገጠሙትን ችግሮች በሰፊው በመመርመር አጠቃላይ ግንዛቤዎችን ወስዷል፥ ውሳኔዎችን አሳልፏል። የኅብረቱን አሠራርና መዋቅር በመመርመር ኅብረቱ ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ የአሠራርና የመዋቅር ማስተካከያዎችን አድርጓል።

### II. ግንዛቤዎች፤

1. የኢትዮጵያ ሕዝብ በመራር ትግሉ የሥልጣኑ ባለቤት ለመሆንና ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ለማድረግ መስዋዕትነት የከፈለበት የግንቦት ፺፯ ምርጫ ውጤት በገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ ከተጭበረበረ ጊዜ አንስቶ ገዥው ፓርቲ ከተራ አምባ ገነንነት ወደ አሸባሪ አምባ-ገነንነት በመሸጋገር ሕጋዊ የትግል በሮችን ከቀን ወደቀን እየዘጋና ሕዝባችንን ታይቶ ለማይታወቅ ሁለንተናዊ ስቃይና መከራ በመዳረግ ለከፍተኛ ትርምስና እልቂት እየዳረገው መሆኑን፥
2. በአንፃሩ ሕዝባችን አንድነቱን ጠብቆ የተቀሙ ድሎቹን ለማስመስ ከዳር እስከዳር የመብት ማስከበር ትግሉን በከፍተኛ ወኔና ቁርጠኝነት መቀጠሉን፥

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ/Tel. 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

ጉባዔው ተገንዝቧል፡፡

**III. ውሳኔዎች፤**

III- 1 የኅብረቱን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ፤

1. የግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም የምርጫ ውጤት በገዥው ፓርቲ በተጭበረበረበትና የሕዝባችን ድምፅ በተሰረቀበት ሁኔታ የኅብረቱ ተመራጮች በሕገ ወጥ መንገድ በተሰየመ ፓርላማ ውስጥ መቀመጫ መያዛቸው የሕዝብን መብት ማረጋገጥና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን የሚያካትተውን የኅብረቱን ዓላማ የሚጻረር መሆኑን በመገንዘብ የኅብረቱ ተመራጮች በፓርላማ መቀመጫ እንዳይዙ የኢዴኃኅ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በአብላጫ ድምፅ የወሰነውን ውሳኔ ሕጋዊነት፥ አግባብነት፥ ወቅታዊነትና ትክክለኛነት አጢኖ የኢዴኃኅ ብሔራዊ ሸንጎ በሙሉ ድምፅ አጽድቆታል፡፡

2. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ውሳኔ በመጻረር የፓርላማ መቀመጫቸውን በያዙና የጋራ አሠራርን በጣሱ የኅብረቱ የቀድሞ የወቅቱ ሊቀ መንበርና የቀድሞ የወቅቱ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀ መንበር ላይ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በኅብረቱ ውስጠ ደንብ አንቀጽ 7.4.1 እና 7.4.2 መሠረት ሁለቱ ተመራጮች ከኃላፊነት እንዲነሱ የወሰደውን ውሳኔ ጉባኤው በቋሚነት አጽድቆታል፡፡

3. ትግሉ ተጠናክሮ ሕዝባችንን የድል ባለቤት ለማድረግ ኢዴኃኅ የተጣለበትን ታሪካዊና ከባድ ኃላፊነት እንዲወጣ ለማስቻል ጉባዔው በኅብረቱ አሠራርና መዋቅር ላይ አስፈላጊ መስተካከሎችን አድርጓል፡፡ አዲስ የኅብረት አመራር አባላትንም መርጧል፡፡

**III-2 የግንቦቱን የምርጫ ውጤት በተመለከተ፤**

1. የኢሕአዴግ ምርጫ ቦርድ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 104/1 በፌዴራልና በክልል የምርጫ ወረዳዎች ነፃና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኛነት እንዲካሄድ ከማንኛውም ተጽእኖ ነፃ የሆነ ምርጫ ቦርድ ይቋቋማል የሚለውን ድንጋጌ በመጻረር በሥልጣን ላይ ካለው ገዥ ፓርቲ ጎን በአድሎአዊነትና በወገናዊነት በመሰለፍ የምርጫውን ሂደት ከዳር እስከዳር የበከለው መሆኑን በመገንዘብ፥
2. በዚሁ ሁኔታ ባጠቃላይ የምርጫው ሂደት የኢትዮጵያን ሕዝብ አመኔታ ባላገኘበትና በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለው ጉጉት በማይመጥን፥ በሌላ በኩል ደግሞ በነፃ ምርጫ ጉዳይ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁትን መስፈርቶች ባላሟላ ሁኔታ የተካሄደ መሆኑን በእርግጥ ገለልተኛ የሆኑ የዓለም - አቀፍ ታዛቢዎች ያጋለጡት ሐቅ መሆኑን በማጤን፤
3. የኢትዮጵያ ሕዝብ የዚህን ምርጫ ውጤት አሻፈረኝ ብሎ ሳይቀበል በትግልና በመስዋእትነት ያገኘው ድል እንዳይረጋገጥ ድምፄ ይከበር በማለት አሁንም ከፍተኛ መስዋእትነት በመክፈል እየታገለ መገኘቱን በመገንዘብ፤

   ሀ) የኢትዮጵያ ሕዝብ የምርጫውን ውጤት እንዳልተቀበለው ሁሉ እኛም ቀደም ሲል የወሰድነውን የግንቦት ፺፯ ምርጫን ውጤት አንቀበልም የሚለውን አቋማችንን በማደስ አሁንም ይኸንን የተጭበረበረ ውጤት እንደማንቀበለው እናረጋግጣለን፡፡

ለ) ከዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብም የዓለም አቀፍ ኅብረተሰብም እንደ ሃቀኛ አድርጎ ካልቆጠረው ምርጫ ፈልቆ የተቋቋመው ፓርላማ የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት በአንቀጽ 54/1 " የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ሁሉን አቀፍ፥ ነፃ ፥ ቀጥተኛና ትክክለኛ በሆነና ድምፅ በምስጢር በሚሰጥበት ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ" ተብሎ የተደነገገውን በመጣስ የአገሪቱን ሕገ-መንግሥት ተጻርሮ የተሰየመ በመሆኑ ይኸ አካል ሕገ-ወጥ መሆኑን ጉባዔው አምኖበታል።

ሐ) ከዚህ ከጥንስሱ ጀምሮ እራሱ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ያወጣውን ሕገ-መንግሥት እንኳን በተፃረረ መልክ የተሰየመ ፓርላማ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 56 እና አንቀጽ 73 መሠረት ተጠቅሞ የፌዴራል መንግሥቱን የሕግ አስፈጻሚ አካል የማደራጀትም ሆነ በምክር ቤት ውስጥ አብዛኛውን መቀመጫ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ ድርጅቶች ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ይመረጣል የሚሉትን አንቀጾች በተግባር ለማዋል የሞራልም ሆነ የፖለቲካ ብቃት ስለሌለው በዚህ ምክር ቤት የተሰየመ መንግሥትም ሕገ-መንግሥቱን በተጻረረ መልክ የተቋቋመ አካል መሆኑን አምነንበታል።

መ) የተቃዋሚ ድርጅቶች ተመራጮች በዚህ አካል ውስጥ መግባት ለአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሂደት ምንም ዓይነት ጠቀሜታ አለመኖር ብቻ ሳይሆን እንዲያውም የሕዝቡን ሰፊር ትግል ግራ የሚያጋባና ሕዝባዊ አጀንዳ ይዘው የሚታገሉትን ኃይሎች ለአፈና የሚያጋልጥ የተሳሳተና አደገኛ እርምጃ መሆኑን ጉባዔው አምኗል።
ይኸን ሕገ-ወጥና ፀረ ሕገ-መንግሥት ሂደት ተቃውመው "የሕዝብ ድምፅ ይከበር" የሚል መፈክር አንግበው በመታገልና በመሰዋት ላይ ያሉት ወጣቶች፥ ተማሪዎች፥ ወላጆች፥ ነጋዴዎች፥ ገበሬዎችና ሠራተኞች እንዲሁም ባጠቃላይ የአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በሙሉ ኃይላቸውን አስተባብረው ከኢሕአዴግ ቁጥጥር ውጭ ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ባሟላ ሁኔታ አዲስ ምርጫ እንዲደረግ የተቀጣጠለው ትግል እንዲፋፋም የአዴኃን ሁለተኛው አስቸኳይ የሸንጎ ጉባዔ ጥሪውን ያቀርባል።

## III-3. የሕዝባችንን የመብት ማስጠበቅ ተጋድሎ ለመደምሰስ በኢሕአዴግ በመካሄድ ላይ ያለውን የሽብር ዘመቻ በተመለከተ፤

1. ዛሬ ሕዝባችን የተቀማ መብቱን በእጁ ለማስገባት ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሶ የሚያካሂደውን ተጋድሎ የኢሕአዴግ መሪዎች፥ በሽብር ዘመቻ ለመጨፍለቅ በሚያደርጉት መፍጨርጨር በነፃው ፕሬስ፥ በተማሪዎች፥ በወጣቶች፥ በተጨነቀ ወላጅ እናቶች፥ በነጋዴዎች፥ በሠራተኞች፥ በምሁራንና በጠቅላላው በዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ላይ ይኸ ነው የማይባል ግፍ እየፈጸሙ መሆናቸውን በመረዳት፥

2. ይኸንን ተገቢ የሕዝብ ትግል አመራር አልባ አድርጎ ለማምከን በቅንጅቱ አመራር አባላትና ደጋፊዎች፥ በኢዴኃን መሪዎች፥ አባላትና ደጋፊዎች፥ በሌሎች የተደራጁ የሲቪክና ሌሎች ስብስቦች አባላትና ደጋፊዎች የግድያ፥ የእስራት፥ የወከባና የአፈና ዘመቻ መክፈታቸውን በማጤን፥

3. የዚህ የሽብር ዘመቻ አንዱ ገጽታው ከግንቦት ፳፯ በፊት በአገሪቱ ውስጥ በሕዝቡ መራር ትግል የተገኙትን፥ በጭላንንጭል ደረጃ የነበሩ መብቶችን ሙሉ በሙሉ የማውደም ሂደት በመሆኑ ዛሬ በነፃው ፕሬስም ሆነ በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ

በተጠያቂነትም ሆነ በሕግ የበላይነት ጥያቄ አገራችን የኋሊት የተጓዘች መሆኗን በማጤን፥

4. የዚህ የኋሊት ጉዞ አስከፊ ገፅታ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ወጣቶች ታፍሰው በየማጎሪያ ጣቢያዎች መወሰዳቸው፥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎች መገደላቸው፥ ከእነዚህ ውስጥ በርካታዎቹ በጅምላ መቃብር መወርወራቸው፥ ምንም ተጠያቂነት በሌለበት ሁኔታ ወላጆችና ዘመዶች ስለጠፉ ልጆቻቸው ምንም መረጃ አለማግኘታቸው፥ ለተሰው ዜጎች እርም ማውጣትን የመሰለ መሠረታዊ መብት መነፈጋቸው መሆኑን በመገንዘብ፥

   ሀ) በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ልጆቻንን ባወጣ ያውጣቸው ብለን ስለማንተዋቸው ወላጆችም፥ የአገራችን ዴሞክራቶችም፥ የአውሮጳ ፓርላማና ሌሎች ዓለም-አቀፋዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በጠየቁት መሠረት የኢሕአዴግ መንግሥት ያሠራቸውን ዜጎች ሁሉ የስም ዝርዝር ይፋ እንዲያደርግ፥ የት እንዳሠራቸው እንዲያስታውቅና፥ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ዛሬ ነገ ሳይል ባስቸኳይ እንዲፈታቸው ጉባዔው አጥብቆ ይጠይቃል""

   ለ) በየጎዳናው ተረሽነው በጅምላ መቃብሮች የተጣሉትና በእስር ላይ እያሉ በአካላዊ/ኅሊናዊ ማሰቃየትና ሰቆቃም (በቶርቸር) ሆነ በሌሎች ምክንያቶች ሕይወታቸው ያለፈ ወጣቶችና ሌሎች ዜጎች የስም ዝርዝር ባስቸኳይ ይፋ እንዲሆንና አስከሬናቸውም ከተጣለበት ጉድጓድ ወጥቶ ለቤተ ዘመድ ተሰጥቶ ሰማእቶቻችንም በክብር እንዲቀበሩ፥ ዘመድ አዝማድም እርሙን እንዲያወጣ ይደረግ ዘንድ ጉባዔው አጥብቆ ይጠይቃል።

   ሐ) የታሠሩ የቅንጅት መሪዎችና አባላት፥ የኢዴኃኅ አባላትና ታጋዮች፥ የነፃው ፕሬስ ባልደረቦች፥ የሲቪክ ማኅበራት መሪዎችና ታጋዮች እንደዚሁም ስፍር ቁጥር የሌላቸው የፖለቲካ እስረኞች ባስቸኳይና ያለ አንዳች ቅድመ-ሁኔታ እንዲፈቱ ጉባዔው አጥብቆ ይጠይቃል።

   መ) በጋምቤላ አካባቢና በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች እየተካሄደ ያለው የጅምላ ግድያ፥ አፈናና ጭፍጨፋ ባስቸኳይ እንዲቆምና ለደረሰውም ግፍ ተጠያቂዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ ጉባዔው አጥብቆ ይጠይቃል።

   ሠ) በሕዝቡ ትግል አካልነት ሳቢያ የንግድ ቤቶቻቸው የታሸጉባቸው ነጋዴዎች ለኅብረተሰቡ መደበኛ አገልግሎቶቻቸውን እንዲቀጥሉ፥ ከሥራ የተባረሩ ወደ መደበኛ ሥራቸው እንዲመለሱ፥ ተማሪና አስተማሪን በገፍ በማፈስ፥ በትምሕርት ቤቶች ቅጥር ግቢ ወታደር በማሰማራት አላስፈላጊ ውጥረትን በመፍጠር ተማሪዎችን ማወክና ትምሕርት ቤቶችን በመዝጋት የመማር ማስተማር ሂደቱን የማኮላሸቱ ተግባሮች ባስቸኳይ እንዲቆሙ ጉባዔው ይጠይቃል።

   ረ) ቀደም ሲል ኢዴኃኅ፥ በቅርቡ ደግሞ የአውሮጳ ፓርላማ በጠየቁት መሠረት በተባበሩት መንግሥታት አስተባባሪነት ከሰኔ ወር ፺፯ ዓ/ም ጀምሮ ስለተፈፀሙት ግፎች ዓለም-አቀፋዊ ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን ባስቸኳይ እንዲቋቋምና ለዚህ ሁሉ ተጠያቂ የሆኑት ወንጀለኞች ለፍርድ እንዲቀርቡ ጉባዔው አጥብቆ ይጠይቃል።

## III- 4 ሽብርን ተቋቁሞ ዴሞክራሲን ለማስፈን የጋራ ትግል ስለማስፈለጉ ፤

1. ዛሬ ሽብርን እየተቋቋመና ከባድ መስዋእትነት እየተከፈለበት በመቀጣጠል ላይ ያለው ትግል በሕዝባችን በኩል ከትግል ወኔውም፥ በመስዋእትነት ዝግጁነቱም ምንም ሳይጎድለው የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የሲቪክና የሙያ ስብስቦች ታሪካዊ ሚናቸውን መጫወት እንዳይችሉ እየተደረጉ ያለበት፥ አገራችንና

ሕዝባችን ለዘግናኝና የባሰ መከራ ዘመን ሊጋለጡ የሚችሉበት አደጋ እንዳለ በጭንቀት በማጤን፤

2. ይኸንን የሕዝብ አጀንዳ ወደፊት የማራመድ ሃላፊነት የዚህ ወይም የዚያ የፖለቲካ ድርጅት፥ የዚህ ወይም የዚያ የሲቪክ ስብስብ፥ የዚህ ወይም የዚያ ግለሰብ ጉዳይ ሳይሆን በመላው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ኃይሎች፥ የሲቪክና የሙያ ስብሰቦችና የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ተማሪዎች፥ ወጣቶች፥ ወላጆች፥ ሴቶች፥ ነጋዴዎች፥ ገበሬዎች፥ ሠራተኞች፥ ዛሬም በአለው ሁኔታ አገራዊ ስሜት ያላቸው የሠራዊትና የፖሊስ ባልደረቦች፥ ወዘተ... በሙሉ የሚተባበሩበት ሁሉን አቀፍ የሆነ ሕዝባዊ ተጋድሎ መሆኑን በመገንዘብ፤

3. ያለንበት የትግል ምዕራፍ ድርጅቶች ለምርጫ የሚወዳደሩበት ሳይሆን ኅብረተሰቡን ከአስከፊ ሽንፈት አትርፎ ዴሞክራሲን የማስፈን የትግል ምዕራፍ በመሆኑ የማንም ይሁን የማን ድርጅታዊ አጀንዳ ስሌት ወይም ፕሮግራም ቦታም ትርጉምም እንደሌላቸው በማመን፤

ሀ) ሸንጎው አገሪቱ ያለችበት እጅግ ፈታኝ የቀውጢ ጊዜ መሆኑን በማጤን ሕዝባችንን ከዳር እስከዳር በማደራጀትና በማንቀሳቀስ የኢሕአዴግ አምባገነናዊ አሸባሪ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያወጀውን የሽብር ጦርነት በጋራ ለመቋቋምና የታሰሩ ዜጎችን ለማስፈታት የፖለቲካ ፕሮግራም፥ የአደረጃጀት፥ የአካባቢ፥ ወዘተ.... ልዩነት ሳይኖር የጋራ እንቅስቃሴ ማድረግ እንዲቻል ከሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች፥ ከሲቪክ፥ ከሙያ ማኅበራትና ልዩ ልዩ ስብስቦች የተውጣጣ አንድ "<u>አገር-አቀፍ የቀውጢ ጊዜ ግብረ-ኃይል</u>" በአስቸኳይ እንዲቋቋም ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ለ) የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ ተንቀሳቅሶ ከኢሕአዴግ አሸባሪና አምባ-ገነን አገዛዝ እየተሰነዘረበት ያለውን የግፍ ጥቃት በጋራ ተቋቁሞ፥ የተረገጡ መብቶቹን በማስከበር ያስመዘገባቸውን ድሎች ማስጠበቅና የተደገሰለትን አጠቃላይ ቀውስና ትርምስ አክሽፎ ለመሠረታዊ ችግሮቹ የሰከነ መፍትሔ ለማስገኘት የሚደረገው ጥረት ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ የኅብረቱ የጠና እምነት ነው። ስለሆነም ከጊዜ ወደ ጊዜ የባሰ እየተወሳሰበ ለመጣው እጅግ አሳሳቢ የአገራችን የቀውስ ሁኔታ በአንድ ድርጅት ወይም በተወሰኑ ድርጅቶች ብቻ በጎ ፈቃድና ጥረት አስተማማኝና ዘለቄታዊ መፍትሔ ማግኘት ስለማይቻል፥ ኅብረታችን ከተመሠረተ ጊዜ ጀምሮ ባለው "ለጋራ ችግር የጋራ ትግል የጋራ መፍትሔ" መተክላዊ እምነት መሠረት የአገሪቱን ሁኔታ በጋራ በመመርመር የወደፊት አቅጣጫን በጋራ ለመተለምና የጋራ ዕድልን በጋራ መክሮ ለመወሰን፥ አግላይነትን ባስወገደና ሁሉንም ባቀፈ መልኩ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት፥ የሐይማኖት ተቋማት፥ የሴቶች፥ የወጣቶች፥ የገበሬዎች፥ የሠራተኞች፥ ወዘተ ... ስብስቦች ተወካዮች የሚሳተፉበት አንድ "<u>ሁሉን አቀፍ አገራዊ ጉባዔ</u>" በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲካሄድ፤ ለዚሁም ተግባራዊነት ዝግጅቱ በጋራ እንዲጀመር ለሁሉም ክፍሎች አስቸኳይ ጥሪ እንዲተላለፍ ጉባዔው ወስኗል። ይኸ አገራዊ ዓላማ እውን እንዲሆን የሁሉንም ቀናና ቀልጣፋ ተሳትፎ ስለሚጠይቅ ለአገር-ወዳዶችና ለዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሁሉ ጥሪያችንን እነሆ እናቀርባለን።

ሐ) የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት በተቋቋመበት መንፈስ የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢሕአዴግ የታወጀበትን የሽብር ጦርነት ተቋቁሞ፥ የተደገሰለትን የትርምስ አደጋ አስወግዶ፥ በተባበረ ትግሉ የኢሕአዴግን

አሸባሪና አምባ-ገነን ሥርዓት አስወግዶ ሕዝቡ የሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ጊዜውና ሁኔታው በሚጠይቀውና በሚፈቅደው መጠን ሕዝባዊ ትግሉን ለመቀጠል ጉባዔው ወስኗል።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥያቄዎች ያቀፉ የኢዴኃን ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ሁለተኛ አስቸኳይ ጉባዔ ውሳኔዎችና ጥሪዎች ተግባራዊ ለማድረግ በውጭም በውስጥም ትግሉ ከአሁኑ ይበልጥ ተጋግዞና ተቀነባብሮ እንዲቀጥል የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ለአገራችን አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሁሉ ጥሪውን በከፍተኛ ወገናዊ ስሜትና አክብሮት ያስተላልፋል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ)

ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም
ዋሽንግተን ዲ.ሲ. አሜሪካ